## የሴቶችን መብት ማስከበር
## የሁሉም ኃላፊነትና ግዴታ ነው

የካቲት 29 ቀን 2004 ዓ.ም.

ለማንኛውም የዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን ታሪክን በጥሞና ለተመለከተ ቅን ሃሳቢ ዜጋ ባለፉት መቶ ዓመታት በዚህ በኩል የተደረጉት እንቅስቃሴዎች ለማህበራዊና ፖለቲካዊ ፍትህ መገኘት የተደረጉ ትግሎች መሆኑን ይገነዘባል። ይህ *የሴቶች ቀን* አንዳንዴም የእናቶች ቀን የሚል ስያሜን አግኝቶ በየካቲት 29 (ማርች 8) ቀን በየአመቱ በመላው ዓለም የሚከበረው፣ በመላ ዓለም ለሚገኙ ሴቶች ሁሉ የተሻለ የሥራና የኑሮ ሁናቴ፤ የሙብት መከበር፤ ...ወዘተ እንዲኖር ዓላማ ያደረገን ትግል ለማክበር የተወሰነ ቀን ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ሴቶችም የዖታ አምሳያቸው ከሆኑት የዓለም ሴቶች አካል ናቸውና፤ የአንድነታቸውም መገለጫ ነውና አሙቺ መስሎ በታያቸው ሁናቴ በየቦታው የሚያከብሩት መሆኑ ግልፅ ነው። እንዲሁም ይህ ቀን ሥርነቀል የሆነ ለውጥ ለማምጣት ሴቶች ያደረጉትን እንቅስቃሴና እንዲሁም ባሕልና ጥረታቸውን ለማስታወስና በተለይም ደግሞ ለዚሁ ዓላማ ሲሉ የተሰዉትን ጀግና ሴቶችንና ታሪካቸውን ለመዘከሪያ እያገለገለ የሚገኘውም መሰረቱ ይኸው ነው። ባለፉት አንድ መቶ አመታት ለጾታ እኩልነት፤ ለሴቶች ነፃነት መጎናፀፍና መብት መከበር ለተደረገውና አሁንም እየተደረገ ያለውን ትግል ለማስታወስ መቶኛ አመቱ ባላፈው ዓመት ተከብሮ እንደነበር ይታወሳል። በቅርቡ ደግሞ 101ኛ ዓመቱ በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች እየተከበረ ይገኛል።

በነዚህ መቶ አመታት በተወሰኑ የዓለም አካባቢዎች በትግል የተገኙ ድሎች ቢኖሩም አሁንም ገና ያልተሟሉ ቀጣይና ያላሰለሰ ትግልን የሚጠይቁ፤ የሴቶችንም በጋራ በአንድነት መቆምንና የወንዱንም ከፍተኛ አጋርነት የሚሹ በርካታ ፖለቲካዊ፤ ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ጥያቄዎች እንዳሉ ግልፅ ነው። አንዳንድ አካባቢ ደግሞ ባለንበት በ21ኛ ምዕተ ዓመት በሴቶች ላይ እየደረሰ ያለው በደልና ጭቆና፤ የከፋና ሀዘን የተሞላበት ከመሆኑም በላይ ኑሯቸው አሰቃቂና አስከፊ መሆኑ በቃላት የሚገለጽ አይደለም። ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን ማክበር ለእነዚህ ክፍሎች ጥብቅና መቆምን መግለፅና ሁኔታቸውን ለሰላምና ፍትህ ወዳድ ኃይሉ ማሳወቅን የሚያጠቃልል ነው። በተለይም በተለያዩ ሀገራት እንደሚታየው በስንት ትግልና ጥረት የተገኙ ድሎች ሁሌም ጥበቃና እንክብካቤ ካልተደረገላቸው እምነትና ባህልን ሽፋን (መሰረት) በማድረግ የሚቀለበሱ መሆናቸው ደግሞ የሚታይ ነው። ምስራቅ አውሮፓ ለዚህ መልካም ምሳሌ ነው። በሰሜን አፍሪካና በሌሎች አረብ ሀገራት አምባገነን አገዛዝንና መሪዎችን ለመጣል በተደረገው ትግል የሴቶች ተሳትፎና የከፈሉት መስዋዕት ከፍተኛ ቢሆንም የትግላቸውን ፍሬ ለመቋደስ የተቸገሩበት ምክንያት የዚሁ የቅልበሳ ነፀብራቅ በመሆኑ ነው።

የካቲት 29 ቀን (March 8) ዓለም አቀፋዊነትን እየተላበሰ የሚገኘው በአለም አቀፍ ደረጃ የተቋቋሙ በርካታ ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚያከብሩት በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለጉዳዩ በሰጠው ትኩረት በ1977 ዓ.ም ባደረገው ጠቅላላ ስብሰባው በዓመት አንድ ቀን "የሴቶች መብትና የሰላም ቀን" በተሰኘ መርሃ መፈክር ተከብሮ እንዲውል በመወሰኑም ጭምር ነው። በሀገራችን በኢትዮጵያም "ያ ትውልድ" ተብሎ የሚጠራው ተራማጅ

ዜጋ የኢትዮጵያ ሴቶችን አስከፊ ሁናቴ አንስቶ መወያይት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ወቅቱ በፈቀደው ደረጃ ሴቶች የራሳቸውን ነፃ ድርጅት እንዲመሰርቱና ለመብታቸው እንዲታገሉ ቀላል የማይባሉ ጥረቶች ማድረጉ ታሪክ የመዘገበው ነው። የዚህ ትውልድ ነፀብራቅ የሆነው ኢሕአፓም ከተመሠረተበት ከዛሬ 40 አመት ጀምሮ እንቅስቃሴዎቹን ባካሄደባቸው አካባቢዎች ሁሉ ለሴቶች መጨቆን አስተዋጽዖ እያበረከቱ ያሉ ጎጂ ልማዶች፣ ወጎች፣ ባሕሎች፣ አመለካከቶች፤ አነጋገሮች፣... እንዲወገዱ በማስተማር ያደረጋቸው ሥራዎች በዚህ የተካፈለው ሕዝብ እራሱ ምስክር ነው። መብታቸውንም በማስከበር ብቻ ሳይሆን በራሳቸው ተደራጅተው እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ፤ በተለያዩ የድርጅቱ ተቋማት ውስጥም የአመራር ኃላፊነት ተረክበው ለሕብረተሰቡ ነፃነት መጎናፀፍና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ያደረጋቸው ጥረቶችና ያስገኛቸው ውጤቶች ለሌሎች አርዓያ የሚሆኑ ከቶም ሊረሱ የማይችሉ የትግሉ ታሪክ ናቸው።

ተራማጅ ነን እያለ ይመፃደቅ የነበረው የደርግ ሆነ የአሁኑ ዘረኛ አምባገነን የመለስ አገዛዝ ሕገ መንግሥታችን በሚሉት ሰነዳቸው ላይ ስለ ሴቶች መብትና ነፃነት የሚገልፁ አንቀጾችን ሸንቁረው መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ቢነዙም፤ በባዕዳን ጥቂት እርጥባን እየተደገፉ እዚህም እዚያም ከሚንቀሳቀሱት ሕዝባዊ ድርጅቶች በስተቀር በሙሉ ልብ ኃላፊነትና ግዴታ ተሰምቷቸው በተጨባጭ የሴቶችን መብት ያስከበሩበት ሁኔታ የለም። የመለስ አገዛዝ ነጋ ጠባ በየአደባባዩና በየመሥሪያ ቤቶች መፈክር  በመስቀል ሕዝብን ከማስቸገርና ከማስጨነቅ በላይ እንዳልሄደ ድርጊቶቹ የሚያጋልጡት ናቸው። ለፆታ እኩልነት ተቆርቋሪ ነኝ እያለ ለጆሮ የሰለቸ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም በአገዛዙ በኩል ለሴቶች የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ በመሆኑ ሴቶች ከወንዱ ጋር ሲነፃፀር በሁሉም መስክ ያላቸው ተሳትፎ እጅግ ወደኋላ የቀረ ነው። በመሆኑም ዛሬ ብዙሃን ሴቶች ከየመድረኩ ተገለውና ተጨቁነው መገኘታቸው (በመለስ ዜናዊ ፈቃድ አንዳንድ ሴቶች በሚኒስትርነትና በዳይሬክተርነት ማዕረግ መሾማቸው የፆታ እኩልነትን የሚገልጽ ባለመሆኑ) ፆታቸውን ተንተርሶ በገጠርም ሆነ በከተማ ኗሪ በሆኑ ሴቶች የሚደርሰው በደል መባባሱ፤ የሚያረጋግጠው አንድ ነገር ቢኖር ይህንን ተጨባጭ ሁናቴ ነው። የኢትዮጵያ ሴቶች በሁሉም ዜጋ ላይ ባጠቃላይ በሚፈፀመው የጋራ ጥቃት ባሻገር በሴትነታቸው ብቻ የሚደርስባቸውን ድርብ ጥቃት ጨርሶውኑ ለማስወገድ ቀርቶ በአግባቡ እንኳን ለመቀነስ አልተቻለም።

አሁንም ድረስ የፆታ እኩልነት በተግባር በሚገባ አልተረጋገጠም። በጣም ጥቂት የሆኑ ሴቶች በራሳቸው ጥረት የሥራ እድል አግኝተው ለመቀጠር ቢችሉም ለተመሳሳይ ሥራ እኩል የደሞዝ ክፍያ አያገኙም። በትዳር የተጎዳኙ ሁለቱም የሥራ እድል አግኝተው የሚሰሩ ቢሆን እንኳ የቤተሰብ ኃላፊነቱ በሴቶች ትከሻ ላይ በመሆኑ ሕጻን ልጆቻቸውን ተንከባክቦ ከማሳደግ ጀምሮ አቅም ያነሳቸው፤ በእርጅናም ምክንያት ጉልበት እያጡ የሚሄዱ ወላጆቻቸውን ጭምር ማሰባሰብና መንከባከብ በዋናነት በሴቶቹ ትከሻ ላይ የወደቀ ነው። አበረታች እየተባሉ የመመፃደቂያ፣ የማደናገሪያ፣ የመደለያ መግለጫዎች በመለስ አገዛዝ አሁንም ድረስ ቢዥጎደጎዱም የቤተሰብ ኃላፊነታቸው እየከበደ እንጂ እየቀለለ ሲሄድ አይታይም። ሴቶች ከቤት ውስጥ ጀምሮ በትምህርት ቤት፣ በሥራ



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ቦታ፣ በጓሮ እርሻ፡ ... በሕብረተሰብ መካከል ለተለያዩ በደሎች የተጋለጡ ናቸው። በጋብቻ መልክ ቁርኝት ባለበትም ወንዶች የገቢ ምንጭ፣ የቤት የበላይና ውሳኔ ሰጪ መሆን በቀጣይነት ያለ በመሆኑ ሴቶች በዝቅተኝነት እንዲታዩ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያደረገ ይገኛል። በተለያዩ ጥናቶች እንደተረጋገጠው ከ85 በመቶ በላይ የሚሆኑ ሴቶች ለቤት ውስጥ የኃይል ጥቃት ሰለባዎች የሆኑበት፤ አካላዊ ደህንነታቸው ለተለያዩ አደጋዎችና በሽታዎች የተጋለጡበት፤ በማህበራዊ ሕይወት ተሳትፎ ደረጃ፣ በኤኮኖሚ አቅም፣ በውሳኔ ሰጪነት ሴቶች ዝቅ ተደረገው የሚታዩበት ሁናቴ ሰፍኖ ያለበት ነው። የትዳር ሕይወትን በአግባቡ ማጣጣም በጣም ከባድ በሚሆንበት ሁናቴ ደግሞ አብሮነቱ ትርጉም የሌለው እርካታም የማይገኝበት በመሆኑ የአካል፣ የመንፈስ፣ የሥነ አዕምሮና የሥነ ልቦና ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሴቶች በተለይ ባለፉት 20 አመታት የመለስ አገዛዝ ባሰፈነው የሞራል ድቀትና የሥነምግባር ብልሹነት የተነሳ ቁጥራቸው በሚያስገርምና በሚያስደንቅ ሁናቴ እየተበራከቱ መሆናቸው በጥናት የተደረሰበት ነው። ድብቅና ግልፅ ሴተኛ አዳሪነት በጣም እየተስፋፋ ነው። ይህ በራሱ አስከፊነቱ አልበቃ ብሎ በአገዛዙ አቀናባሪነትና ድጋፍ ሰጪነት በአረብ ሀገር ለዘመናዊ ባርነት እየተዳረጉ ያሉ ወጣት ሴቶቻችን ከድብደባ ጀምሮ ለተለያዩ ጥቃቶች እየተጋለጡ መገኘታቸው በተደጋጋሚ የተገለፀ ነው። ኢሕአፓ ይህንን በሴቶች ላይ እየደረሰ ያለውን ድርብ ጭቆናና በደል አጥብቆ ይቃወማል፤ ያወግዛልም።

ይህ ሥር የሰደድ ችግር ከጠቅላላው የሕብረተሰቡ ሁለንተናዊ ችግሮች ተለይቶ ለብቻው መፍትሄ እንደማያገኝ ኢሕአፓ ፅኑ እምነቱ ነው። ስለዚህም መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ ለማስገኘት ለዴሞክራሲና ለሰብዓዊ መብት መከበር የቆሙ ዜጎች ሁሉ ይህንን በሚገባ ተገንዝበው የመለስ አገዛዝን ከሥልጣን ለማባረር ይቻል ዘንድ የጋራ የትግል ጥሪ በትግሉ ሜዳ እንዲመሠረት ደግሞ ደጋግሞ ያቀርብላቸዋል። የዓለም አቀፍ የሴቶች ቀንን በዛሬው እለት ስናከብረውና ሴት ጀግኖቻችንንም ስንዘክራቸው ባለፉት መቶ ዓመታት የትግል ሂደት ውስጥ ገና በአግባቡ መፍትሄ አላገኙምና ለስኬታማነታቸው ከሴት እናቶቻችን፣ እህቶቻችን፣ ልጆቻችን ጋር በመሆን በፅናት እንታገል ይላል። ሴቶችም ለመብታቸው እንዲታገሉ ነፃ ድርጅታቸውን እንዲያቋቁሙ፤ የተቋቋሙትም እንዲጠናከሩና እንዲተባበሩም ጭምር በሙሉ ልብ እንርዳ፣ እንደግፍ ሲል ኢሕአፓ የጠበቀ አደራውን ያስተላልፋል። ኢሕአፓ የሴቶች ጥያቄ የትግላችን እ

እምብርት መሆኑን እያረጋገጠ፤ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ሲከበር የሚያስተላልፈው ልዩ መልዕክትም አንድ ብቻ ነው። መደራጀት፡ እየተደራጁም መተባበርና መታገል! - የወቅቱ መርሃ ግብር ነው።

የሰቶች መብት ይከበር! የሴቶች ትግል ይጠናከር!
በሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎና ትግል እውነተኛ ድል ይገኛል!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France